# የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ምርጫና የዝሆኖቹ ግፊያ

በነብዩ ተድላ

ቀጣዩን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እንድታስተናግድ ትጠበቅ የነበረችው ማላዊ ነበረች፡፡ በስብሰባው ላይ በዓለምአቀፉ የወንጀለኞች ፍ/ቤት (ICC) በሱዳን ዳርፉር ተፈፀመ በተባለ የጦር ወንጀል ምክንያት ክስ ተመስርቶባቸው የሚገኙት የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኦማር ሀሰን አልበሽር ወደ ማላዊ እግራቸው የሚረግጥ ከሆነ እንደ ዓለምአቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ወንጀለኞችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ፈራሚነቴ ፕሬዚዳንቱን ባስተናገድ ኃላፊነቴን ከመወጣት ወደኋላ ብለሻል ተብዬ መወቀስ አልሻም የሚል መግለጫ አገሪቱ አውጥታለች፡፡ የአፍሪካ ህብረት በሱዳን ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ ቀውስ ወደ ተባባሰ ማጥ ላለመክተት የፕሬዚዳንቱ ክስ ለጊዜው እንዳይታይ ቀደም ሲል መጠየቁና ማላዊም በቅርቡ በአገሯ በምታስተናግደው ጉባኤ ላይ ለፕሬዚዳንቱ ቀዩን ምንጣፍ እንድታነጥፍ መጠየቁ ይታወሳል፡፡ የአገሪቱ የቀድሞ ፕሬዚዳንትና በቅርቡ ሚያዝያ ላይ ህይወታቸው ያለፈው ሲንጉ ዋ ሙታሪካ የበሽርን አሳልፎ መስጠት እንዴት ተደርጎ ሲሉ ተቃውመውት እንደነበር ይታወሳል፡፡

ሚቹን ፕሬዚዳንት የተኩት ጆይስ ባንዳ አገራቸው ለአፍሪካ ህብረት ያላትን ኃላፊነት ያህልም ለሌሎች ዓለምአቀፍ ተቋማት ያለባት መሆኗን በመግለፅ በተለይም ከአንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገሮችና ተቋማት በኩል የሱዳኑን ፕሬዚዳንት አሳልፈው እንዲሰጡ ጉዳይ ጫና እየተደረገባቸው መሆኑን ከመግለፅ ወደኋላ አላሉም፡፡ አገራችን ቀደም ሲል በዚሁ ጉዳይ ዳኅስ ያለ የልማት ድጋፍ አጥታለች፡፡ አሁንም በበሽር ምክንያት ይህንን ጎን ጠግን እርዳታ ለማጣት አቅሟ አይፈቅድም ሲሉ የአገሪቱ ባለሥልጣናት ሲገልጹ ተደምጧል፡፡

በሄግ ተቀማጭ የሆነውን የዚሁ ፍርድ ቤት የእስር ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ላይ ታች ደፋ ቀና ሲሉ የቆዩት ሉዊስ ሞሬኖ ኦካምፖ የሥራ ዘመናቸው በዚህ ወር ከመገባደዱ በፊት በሽርን በእግረ ሙቅ ለማሰር ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት አንፃር እንደሆነ የተነገረለትና በሽርን በአገራቸው የሚቀበሉ መንግስታት ከማንኛውም ዓለምአቀፍ የልማት እርዳታና ድጋፍ ተርታ መውጣት አለባቸው ሲሉ መናገራቸው በብዙዎች ጉዳዩን ኦካምፖ የግለሰብ ጠብ አደረጉት እንዴ እስከማለት አድርሶባቸዋል፡፡ የማላዊም ውሳኔ የዚህን መሰል ቅጣት ፍራቻ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፡፡

በእርግጥ የአልበሽር ክስ በብዙዎቹ የአፍሪካ ህብረት አባል አገራትና ለሱዳን ሠላም በሚሠሩ ዓለምአቀፍ አካላት ዘንድ የሀሳብ መለያየትና የሠላ ክርክር ውስጥ ማስገባቱ

ይታወሳል፡፡ ብዙ የICC አባል አገሮች ምንም እንኳ የተቋሙ ፈራሚ አባሎች ቢሆኑም የፕሬዚዳንት አልበሽር መከሰስ በሱዳን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰው የሠላም ማስፈን ጥረት ላይ አደጋ መደቀን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ክሱ በምዕራባውያን በኩል የተቀነባበረና በሽርን ለማስወገድ የሚደረግ የፖለቲካ ሴራ ነው የሚሉትን ጨምሮ፡፡

የአፍሪካ ህብረት አባል አገራት ከጽ/ቤቱ መቀመጫ ውጭ የሚካሄዱ የህብረቱን የመሪዎች ጉባኤዎችም ይሁኑ ሌሎች ለማስተናገድ ሲመረጡ ስብሰባውን እንዲያካሂዱ የተመረጡ አገሮች መንግስታት በራሳቸው ውሳኔ ብቻ በመመስረት በስብሰባው ማን ይሳተፍ ማንስ አይሳተፍ የሚለውን ውሳኔ መወሰን ከጀመሩ፣ እንዲህ መሰል ውሳኔዎችም በህብረቱ የጋራ ውሳኔ (Unanimous Decision) መወሰኑ ቀርቶ በተናጠል የስብሰባ አዘጋጅ አገሮች የሚወሰኑት ከሆነ የስብሰባ አዘጋጅነት ኃላፊነትና ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀም እንዳይሆን ያሰጋል፡፡ ቀደም ሲል የአፍሪካ ህብረት በጋራ ውሳኔው በህብረቱ ስብሰባዎች ላይ እንዳይሳተፉ በጊኒ፣ በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክና በኒጀር ላይ እገዳ መጣሉ አይረሳም፡፡ አሁን ደግሞ ተመሳሳይ እገዳ በማዳጋስካር፣ ማሊና ጊኒ ቢሳው ላይ ማስተላለፉ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እንዲህ መሰል ውሳኔዎች በህብረቱ አሉታዊ የፓለቲካ፣ የህግና የዲፕሎማሲያዊ አንድምታዎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት ግን የአፍሪካ ህብረት ከተቋቋመበት አላማዎች አንዱ ለሆነው የዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን፣ ዲሞክራሲያዊ ባህልንና ተቋማትን፣ ህዝባዊ ተሳትፎዎችን መልካም አስተዳደርንና የመሳሰሉትን አያስተናግድ ማለት እንዳልሆነ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያምናል፡፡ ለዚህም ይመስላል ይህን ጉባኤ ማላዊ እንደማታስተናግድ በመግለጽ ስብሰባውን የማስተናገድ ኃላፊነት የጽ/ቤቱ መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ እንድትቀበል የተደረገው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ተንታኞች ከፖለቲካ አንድምታው በላይ ማላዊ ከፍተኛ ቁጥር ያለው እንግዳ የሚሳተፍበት የአፍሪካ ህብረት የመሰለ ጉባኤ ለማስተናገድ የሚያስችል አጠቃላይ የሎጂስቲክስ አቅሙ ስለሌላት በአልበሽር ምክንያት ስብሰባውን ላለማስተናገድ ሰበብ መፍጠሯንም ይገልጻሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ግን በማላዊ ሊሎንግዌ ከተማ ከጥቂት ሣምንታት በኋላ እንዲካሄድ ይጠበቅ የነበረውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ የህብረቱን ጉዳዮች በቅርበት ለሚከታተሉ ሁሉ ይበልጥ አጓጊ አድርጎት የነበረው ጉዳይ በስብሰባው ላይ እንዲካሄድ ቀጠሮ የተያዘለት የህብረቱን ኮሚሽን ሊቀመንበር ለመምረጥ ለ2ኛ ጊዜ የሚካሄደው ምርጫ ነበር፡፡

እንደሚታወሰው በጥር ወር አዲስ አበባ ላይ ተካሂዶ በነበረው 18ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ወቅት ለህብረቱ ኮሚሽን አዲስ ሊ/መንበር ለመምረጥ አባል አገራት ምርጫ አካሂደው የነበሩ ቢሆንም ጋቦናዊው የወቅቱ የኮሚሽኑ ሊ/መንበር ዶ/ር ዣን ፒንግ እና ደቡብ አፍሪካዊቷ ዶ/ር ንኮሳንዛ ድላሚኒ ዙማ የማሸነፊያውን ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ለማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ዶ/ር ፒንግ ከዚህ ቀደም እንደነበሩት የህብረቱ ኮሚሽን ሊቃነመናብርት ሁሉ ለሁለተኛ ዙር የሥራ ዘመን ለመመረጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ሲጀምሩ ነው ባልተጠበቀና የህብረቱን የዚህ ቀደም ልማድ፤ ማለትም የአፍሪካ አህጉር ታላላቅ አገራትና የህብረቱ ቀዳሚ ደጋሚዎች በተለይም ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ሊቢያ፣ አልጄሪያና ግብፅ እንዲሁም የጽ/ቤቱ መቀመጫ የሆነችው ኢትዮጵያ ለሊቀመንበርነቱ ቦታ መወዳደር አይኖባቸውም የሚለውን ልማዳዊ ግን ያልተፃፈ ህግ (The Gentlemen's Agreement) ወደጎን በማድረግ የደቡብ አፍሪካ መንግስት የአገሪቱን ፕሬዚዳንት ጃኮብ ዙማ የቀድሞ ባለቤትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአሁኗ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ዙማን ዕጩ አድርጎ ያቀረበው፡፡

ይህ ሁኔታ በህብረቱ አባል አገራት ውስጥ ትልቅ የምርጫና የፖለቲካ ልዩነትና ቀውስን አስከትሏል፡፡ በዚሁ ምክንያት የሥራ ጊዜያቸው የተገባደዱ የህብረቱ ም/ኮሚሽነርና የተቋሙን የተለያዩ ዘርፎች የሚመሩ የስምንት ኮሚሽነሮች ምርጫም እንዲራዘም የተደረገው፡፡ ይህን ቀውስ ተከትሎም ህብረቱ ለጉዳዩ እልባት ለማግኘት ምርጫውን ለጊዜው በማቋረጥ የኢትዮጵያውን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጨምሮ 8 የአገራት መሪዎች ያሉበት ኮሚቴ እንዲቋቋምና በህብረቱ አንድነት ላይ ችግር የደቀነውን የዚህ ምርጫ ጉዳይ እልባት እንዲያስገኙ ኃላፊነት የሰጠው፡፡ ሆኖም የጋቦንና በተለይም የደቡብ አፍሪካ መንግስታት ዕጩዎቻቸውን እንደማያነሱ ቁርጥ አቋም በማሳየታቸው ችግሩ እንዳለ እንዲቀጥልና የሊሎንግዌው የመሪዎች ስብሰባ በጉጉት እንዲጠበቅ አድርጐታል፡፡

ቀደም ሲል አዲስ አበባ ላይ በሦስት ዙር ተደርጐ በነበረው የኮሚሽነሩ ምርጫ ሦስቱንም ዙር ዶ/ር ፒንግ አብላጫ ድምፅ ያገኙ ቢሆንም የማሸነፊያውን ሁለት ሦስተኛ ድምፅ እንዳያገኙ በተለይ የደቡብ አፍሪካዋን ዙማ የሚደግፉ አገሮች በመጨረሻው ዙር በደንቡ መሠረት ድምፃቸውን ለፒንግ መስጠት ሲገባቸው ድምፀ ተአቅቦ በማድረግ ፒንግ እንዳያሸንፉ ማድረጋቸው በህብረቱ ፖለቲካዊ አንድነት ላይ ብዙዎችን ጥያቄ እንዲያስነሱ ያስገደደው፡፡ ደቡብ አፍሪካና የደቡባዊ አፍሪካ አገራት ዶ/ር ዣን ፒንግ በዙማ መተካት ይኖርባቸዋል ሲሉ አንዳንድ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት፣ ናይጄሪያን ጨምሮ በርካታ

የምዕራብ አፍሪካ አገራት ደግሞ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሁሉ ዣን ፒንግ ለሁለተኛ ጊዜ የመመረጥ መብታቸው ሊነፈግ አይገባም ሲሉ አቋማቸውን ያሳወቁት፡፡

በአብዛኞች የአህጉሩ ፖለቲከኞችና ዲፕሎማቶች ዘንድ እንደሚገለጸው የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኃያላን አገሮች አህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ ተቋማትን የመቆጣጠር ፍላጎት የአፍሪካ ህብረቱንና አህጉሪቱን ወደኋላ መጎተቱ አይቀርም፡፡ በዚህ ምክንያት ህብረቱ እንደ ህብረት በጋራ ድምፅ አመራሮችን መምረጥ አለመቻሉና ካለፈው ጥር ወር ጀምሮ በዚህ ጉዳይ 'ኮማ' ውስጥ መግባቱ በህብረቱ አላማዎች ተፈፃሚነት ላይ መጓተትን ከመፍጠሩም ባሻገር የአፍሪካ ህብረትንና አባል አገራቱን ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የሚያይበት አይንና የሚቀበልበት ልብ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

የናይጄሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኦሉግቤንጋ አሺሩ በቅርቡ ለመገናኛ ብዙሀን በሰጡት መግለጫ የደቡብ አፍሪካን ዕጩ ሆኖ መቅረብ አገራቸው እንደማትደግፈውና ይልቁንም የሊቀመንበርነት ቦታውን በትንንሽና መካከለኛ ለሆኑ የአፍሪካ አገራት ሊሰጥ እንደሚገባ ይህም ሀገራቱ ለአህጉሩ ተቋም የኔነት እንዲሰማቸው ብሎም ታላላቅ አገራት አላስፈላጊ ጫና በህብረቱ ላይ እንዳያሳድሩ እንደሚያደርግ መከራከራቸው ደቡብ አፍሪካ ለቦታው ዕጩ ማቅረቧ በብዙዎቹ የአፍሪካ አገራት እንዳልተወደደ መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በጉዳዩ ላይ ያለውን የሰፋ ልዩነት በበላይነት እየመሩ ያሉት የሚመስለው የደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ ዲፕሎማሲያዊ ፍትጊያ ግን ጎልቶ ወጥቶ የአፍሪካውያንን ተረት "ዝሆኖች ተጣልተው..." የሚለውን እንዳይፈጥር ያሰጋል፡፡

## የደቡብ አፍሪካ መከራከሪያ ነጥቦች

በጉዳዩ ዙሪያ ከደቡብ አፍሪካና የአካባቢው አገራት እየተሠነዘረ የሚገኘው የመከራከሪያ አመክንዮ የአፍሪካ ህብረት በ50 ዓመት ዕድሜው የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ (ሳዴክ) ተወካይ አገር ሲመራው አልነበረም፤ ስለሆነም ጊዜው የክልሉ ነው የሚል ሀሳብ ይቀርባል፡፡ በዚህ የመከራከሪያ ሀሳብ መነሻነትም ደቡብ አፍሪካ የደቡባዊ አፍሪካ አገሮችን በመወከል ዕጩ አቅርባለች፡፡ ዕጩዋን የሳድክ አባል አገራት በሙሉ ድምፃቸው መደገፋቸውም ይነገራል፡፡ ለአብነትም የሳዴክ የወቅቱ ሊቀመንበር አንጎላ ዶ/ር ዲላሚኒ ዙማ እንዲመረጡ የማግባባት ሥራ ለሚሠራው ቡድን የሁለት መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር መመደቧ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን ይገለጻል፡፡ በተለይ ከአንጎላ፣ ናሚቢያ፣ ታንዛኒያ፣ ሞዛምቢክና ዛምቢያ የተውጣጡ የልዑካን ቡድኖች በተለያዩ የአፍሪካ ዋና ከተሞች

እየተዘዋወሩ ዕጩዋቸውን ለማስመረጥ የሚያደርጉትን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ለማገዝ እንደሚረዳ ይታመናል፡፡ ቡድኑ ከምርጫው በፊት ወደ ሴራሊዮን፣ ሴኔጋል፣ ግብፅ፣ ጊኒቢሳው፣ ቶጎ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ቡርኪናፋሶ፣ ሊቢያ፣ ቱኒዝያ፣ ሞሮኮና አልጄሪያ ለዚሁ ተግባር እንደሚንቀሳቀሱ ይጠበቃል፡፡ ምንም እንኳ ዚምባብዌን የመሰሉና ከፕሪቶሪያ መንግስት ጋር አንዳንድ ፖለቲካዊ አለመግባባቶች ያላቸው አገሮች የተለየ አቋም እንደሚያራምዱ ቢታማም፡፡

ሌላው የደቡብ አፍሪካ የመከራከሪያ ነጥብ ከደቡባዊ አፍሪካ ክልል አልፎ ደቡብ አፍሪካ እንደሀገር ቦታውን ለመረከብ ከዚህ ቀደም ምንም አይነት ፍላጎትና እንቅስቃሴ አለማድረጓና አሁን ዕድሉ ሊሰጣት እንደሚገባ የደቡብ አፍሪካ የወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማይቴ ንኮና ማሻባኔ ይገልጻሉ፡፡ እንደሚኒስትሯ አባባል ደቡብ አፍሪካ ተራማጅ ህገመንግስታዊ ዲሞክራሲ በመሆኗ፣ የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖለሲ በአገር ውስጥ እሴቶች የሚመራና ለአፍሪካ አህጉር መሻሻልና መበልፀግ ያለመ በመሆኑ የአፍሪካን ህብረት ለመምራት የሞራልና ፖለቲካዊ ዋስትናቸው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንደሚኒስትሯ ገለጻ አፍሪካ ነፃ ከወጣች በኋላ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት ለአህጉራቸው ቅድሚያ ተጠሪ ከመሆን ይልቅ ለቀድሞ ቅኝ ገዢዎቻቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ በሚል የምዕራብ አፍሪካውያን በተለይም የጋቦንንና የፈረንሳይን ግንኙነት ተቺ የሚመስል ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም ይህ መስተካከል የሚገባው ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ በአፍሪካ አሁን እየታየ ካለውና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተያይዞም ይህን ዕድገት ለማስቀጠልና ፈተናዎችን፤ በተለይም ከቅኝ አገዛዝ ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ልዩነቶችን በማስተካከል ረገድ የደቡብ አፍሪካ ዕጩነት ተገቢ እንደሆኑ ይከራከራሉ፡፡ በዚህም የአፍሪካ ህብረት ብዙ መሻሻሎችን ሊያመጣ እንደሚችል በእርግጠኝነት ሚኒስትሯ ያስቀምጣሉ፡፡

ዶ/ር ድላሚኒ ዙማ በታቦ ምቤኪ ዘመን በነበራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት የሥራ ዘመን ወቅት በአፍሪካ ዛሬ ትኩረት የሚሰጣቸውን የእኩያ መገማገሚያ ስርዓት (Peer Review Mechanism) እና ኔፓድን የመሰሉ ስርዓቶች ሥር በማስያዝ ለአፍሪካ ተሀድሶ ትልቅ ሚናን የተጫወቱ አንጋፋ ዲፕሎማት መሆናቸውን ደቡብ አፍሪካውያኑ ደጋግመው ይገልጻሉ፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ይህን ሀሳብ ይጋራል፡፡ በዚህ ረገድ እንቅልፍ አልፎ አልፎ የሚጫጫነውን የአፍሪካ ህብረት ተቋም ይበልጥ ከማነቃቃት አኳያ ግለሰቧ ትልቅ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል አይካድም፡፡ ችግሩ በግለሰቧ አማካኝነት ድብቅ ብሔራዊ ፍላጎቶችን ለማስፈፀም በላካቸው ሀገር ዘንድ የጫወታ ካርድ መምዘዝ የተጀመረ እንደሆነ ነው፡፡

የደቡብ አፍሪካ መንግስት ዶ/ር ዙማን ለማስመረጥ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ የመሆኑን ሌላ ምክንያት ሳይመን አሊሰን የተሰኙት በጆሀንስበርግ የአፍሪካ ፓለቲካ ተንታኝና በሶማሌላንድ የፈረንሳዩ የአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የቀድሞ ዘጋቢ ሲጠቅሱ ዶ/ር ድላሚኒ ዙማ በደቡብ አፍሪካ የውስጥ ፖለቲካ ተወዳጅነትን እያተረፉ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ ለሁለተኛ የስልጣን ዘመን ለመወዳደር ዝግጅት እያደረጉ ባሉት የቀድሞ ባለቤታቸውና የአገሪቱ የወቅቱ ፕሬዚዳንት ጃኮብ ዙማ ዘንድ በጥሩ አይን አለመታየቱና ፍራቻን መፈጠሩ ነው። በሌላ በኩልም ጃኮብ ዙማ ፓርቲያቸው ከስልጣን ያለግዜ ያባረራቸውና ለአፍሪካ ህዳሴ በህብረቱ አማካኝነት ብዙ አስተዋፅኦ እንዳበረከቱት የቀድሞ ፕሬዚዳንት ታቦ ምቤኪ ሁሉ ለአፍሪካ የሠራ መሪ መባልን ፕሬዚዳንት ዙማ መፈለጋቸውና እንደአንድ የመወዳደሪያ ነጥብ ለቀጣዩ የአገር ውስጥ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ለመጠቀም ማሰባቸውን አሊስን ይጠቅሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ለሁሉም የአፍሪካ ጉዳዮች ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ በቅድሚያ ደቡብ አፍሪካን ማማከር ይኖርበታል የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ደቡብ አፍሪካ እየሞከረችና የፖለቲካ ጡንቻዋን የማፍታታት ፍላጐቷን የሚያሳይ እንደሆነም እኚሁ ተንታኝ ይገልጻሉ።

በመጨረሻም ምናልባት ደቡብ አፍሪካ ዕጩዋን ማንንም አፍሪካዊ አገር ሳታማክር ልማድ ሰብራ ስታቀርብ ዕጩዋ በአፍሪካ አህጉር ካላቸው ታዋቂነት አንፃር በቀላሉ ያሸንፋሉ የሚል እምነት በደቡብ አፍሪካ በኩል የነበረ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ጉዳዩ ደቡብ አፍሪካውያን እንዳሰቡት አለመሆኑ ግልፅ እየሆነ ሲሄድና የፕሬዚዳንት ዙማ መንግስት ጥፋቱ ሲገባው ጉዳዩን ወደኋላ ለመመለስ የማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የመንግስታቸውም ይሁን የአገራቸው ብሔራዊ ኩራት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በመስጋታቸው በዶ/ር ድላሚኒ ዙማ ዕጩነት የደቡብ አፍሪካ መንግስት ሸንጡን ገትሮ እንዲከራከር እንዳደረገው መላምቶች ይሠነዘራሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ዶ/ር ድላሚኒ አገራቸውን በውጭ ጉዳይና በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቀደም ሲልም በጤና ጥበቃና በሌሎች ከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ላይ በማገልገል ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣት እንደሚችሉ ከማስመስከራቸው በላይ ለሴትነታቸው ሲባል ቦታው ለእሳቸው እንደሚገባ የሥርዓተ ፆታን ካርድ በማንሳት የደቡብ አፍሪካ ባለሥልጣናት ይከራከራሉ። ከኮሚሽነር መመረጥ ጋር ተያይዞ ያለውን የአህጉሪቱን የአቋም መከፋፈል ደግሞ እንደ አንድ ግልፅ ዲሞክራሲያዊ የትግል አማራጭና ዕድል ምርጫን የማሳወቅ ሂደት ሊታይ እንደሚገባ እንጂ አፍሪካዊ ተቋሙን ከመበታተን አቅጣጫ

ሊታይ እንደማይገባ የደቡብ አፍሪካዋ የወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማሻባኔ የመንግስታቸውን አቋም አስረድተዋል፡፡

## ናይጄሪያ–ደቡብ አፍሪካ ፍትጊያ

ናይጄሪያና ደቡብ አፍሪካ በአፍሪካ አህጉር ካላቸው አንፃራዊ የኢኮኖሚ ኃያልነት ሁለቱ ታላላቅ የአፍሪካ አናብስት እየተሰኙ በብዙዎች ሲጠቀሱ ይሰማል፡፡ ሆኖም አገራቱ ጠንካራ ሊባል የሚችል የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትስስር የፈጠሩትን ያህል በሁለቱ አገሮች መሀከል መቃቃር ሊፈጥሩ የሚችሉ አንኳር ጉዳዮችም በውስጣቸው እንደለ ይጠቀሳል፡፡

በዚህ ጉዳይ በደቡብ አፍሪካ የአል–ሁዳ መፅሔት ማኔጂንግ ኤዲተርና የአገሪቱ የፖለቲካ ዜና ሐተታና ትንታኔ ሚዲያ የሆነው Daily Maverick ድረ–ገፅ ቋሚ አምደኛ የሆኑት ከዲጃ ፓቴል ሲገልጹ ደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ በአህጉራዊ ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ብዙም ተናበው የማይሄዱ አገሮች እንደሆኑና በአፍሪካ የፖለቲካ ሥነምህዳር ላይ ሁለቱም የየራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ የሚሞክሩ አገሮች እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1995 የናይጄሪያ የአካባቢና ሰብዓዊ መብት ተሟጋች የነበሩት ኬን ሳሮዊዋ አማሟት ጋር ተያይዞ የወቅቱ የሁለቱ አገራት መሪዎች ኔልሰን ማንዴላና ሳኒ አባቻ አይን ለአይን አይተያዩም ነበር፡፡ ሆኖም በሁለቱ አገሮች እ.ኤ.አ. በ1999 በአሉሴጉን ኦባሳንጆና ታቦ ምቤኪ የሚመሩ አዲስ መንግስታዊ አስተዳደሮች ከመጡና መሪዎቹ ኔፓድን በመሰሉ አህጉራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ተናበው መሄድ መጀመራቸው ከአገራቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት መሻሻል የዘለለና ለአህጉራዊ መነቃቃት መፈጠር እድሎችን ካመቻቹ የአፍሪካ መሪዎች መሀከል እንደሆኑ ከዲጃ ፓቴል ይጠቅሳሉ፡፡ ሆኖም ደብብ አፍሪካ ለናይጄሪያ ባለሥልጣናትና ዲፕሎማቶች ቀደም ሲል ሁለቱ አገሮች አቋቁመውት በነበረው የሁለትዮሽ ኮሚሽን መሠረት ትሰጥ የነበረውን ካላቪዛ ወደ አገሪቱ የመግቢያ ፈቃድ እ.ኤ.አ. በ2009 መልሳ ማጠፏ በናይጄሪያ በኩል ቅያሜን አሳድሯል፡፡

በደቡብ አፍሪካ የቪትስ ዩኒቨርሲቲ የዓለምአቀፍ ግንኙነት ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር ጊልበርት ካዲጋላ በበኩላቸው የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ሁሌም በኢሚግሬሽን ጉዳይ ጥላ ያጠላበት እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ በቅርቡም ደቡብ አፍሪካ 125 የሚሆኑ ናይጄሪያውያን የአውሮፕላን ተሳፋሪዎች ከጆሀንስበርግ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በቂ የቢጫ ወባ ክትባት ማስረጃ አልያዛችሁም በሚል ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መደረጉና ናይጄሪያ በበኩሏ ከአገሯ 30 ደቡብ አፍሪካውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ማድረጓን ተከትሎ

የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ጉዳዩ በተሻለ መንገድ ሊያዘ ይችል ነበር በማለት ይቅርታ መጠየቁ ይታወሳል። እነደ ብዙዎቹ ተንታኞች ደቡብ አፍሪካ የጤናን ጉዳይ ፖለቲካዊ አንድምታ በማስያዝ አላስፈላጊ ርቀት እንደተጓዘች ይጠቅሳሉ። ለደቡብ አፍሪካ ነፃነት ከታገሉት አፍሪካውያን መካከል አንዷ ለሆነችው ናይጄሪያም ይሁን ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ደቡብ አፍሪካ እያሳየች ያለው አላስፈላጊ ባህሪ ተገቢ እንዳልሆነም የናይጄሪያ ባለሥልጣናት ይገልጻሉ።

የሁለቱ አገሮች ፍትጊያ ግን ከኢሚግሬሽን ጉዳይ ባለፈ በአፍሪካ አህጉር ጎልቶ የወጣ የፖለቲካ ልዕልና ያላቸው አገሮች ለመሆን በሚደረጉ ትግሎችም እንደሚገለጽ ፕሮፌሰር ካዲጋላ ይጠቅሳሉ። አክለውም ሁለቱም አገሮች በተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ መሻሻል እንዲኖርና አፍሪካን የሚወክሉ ቋሚ ወንበር ያላቸው አገሮች እንዲገቡ ይጠይቃሉ። በተለይ በአሜሪካ በኩል ከደቡብ አፍሪካ ባለፈ ናይጄሪያን የዚሁ ተቋም አባል እንድትሆን የመፈለግ አዝማሚያ መኖሩን ተከትሎ መፋተጉ እያየለ መሄዱን ይጠቅሳሉ። የአፍሪካ ህብረት የኮሚሽነር ምርጫ ላይም ደቡብ አፍሪካ ሳይጠበቅ ድንገት ዕጩ የማቅረቧ ጉዳይ በናይጄሪያ በኩል ቅሬታን የፈጠረውም ይህንኑ ተቋም ተጠቅሞ ለተመድ የፀጥታው ምክር ቤት አባልነት ለመመረጥ ለሚደረግ አላማ ሊውል ይችላል ከሚል ስጋት እንደሆነም ፕሮፌሰሩ ይጠቅሳሉ። በዚህም በተለይ ደቡብ አፍሪካውያን ከዚህ ቀደም የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽንን የመምራት ሚና ለደቡብዊ አፍሪካ አገሮች አልተሰጠም የሚለውን አቋም ታንዛኒያ እንደ ሳዴክ አባል አገርነቷ ደቡብዊ አፍሪካን በመወከል ለ12 ዓመታት ሳሊም አህመድ ሳሊም በሦስት ዙር ተቋሙን መምራታቸውን ናይጄሪያኖችና ሌሎችም የደቡብ አፍሪካን ዕጩ ማቅረብ የሚቃወሙ ሀገሮች እንደመከራከሪያ እያቀረቡት መሆኑን ያስረዳሉ።

የሁለቱ አገሮች መቆራቆስ በተለይ በናይጄሪያ በስፋት ለተሠማሩ የደቡቡ አፍሪካ የቢዝነስ ተቋማት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል የአገሪቱ ባለሀብቶች ከወዲሁ ስጋታቸውን በመግለፅ ላይ ይገኛሉ። በቅርቡ በሌጎስ ይካሄድ በነበረ ዓለምአቀፍ የፋሽን ትርዒት ላይ የደቡብ አፍሪካ ዲዛይነሮች እንዳይካፈሉ መከልከላቸውንም ለዚሁ ክርክር እንደአብነት ይጠቅሳሉ። የናይጄሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሉግቤንጋ አሺሩ በቅርቡ እንደገለጹትም በናይጄሪያ የተሰማሩ የደቡብ አፍሪካ የንግድ ተቋማት ብቃትና ልምድ የሌላቸውን ደቡብ አፍሪካውያን ወደ ናይጄሪያ እያመጡ የናይጄሪያውያንን የሥራ ዕድል የሚዘጉ ከሆነ እገዳ እንደሚጣልባቸውም ማሳወቃቸው የጉዳዩን አሳሳቢነት ገሀድ ያወጣዋል። የደቡብ አፍሪካው የቴሌኮም ተቋም MTN እና የሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ሰጪው DSTV እንዲሁም

Standard Bank በናይጄሪያ እጅግ ከፍተኛ ገበያ እንዳላቸው ይጠቅሷል፡፡ ለዚህም ይመስላል የደቡብ አፍሪካ መንግስት ም/ፕሬዚዳንትን ኻሌማ ሞትላንቴን ወደ ናይጄሪያ በመላክ ጉዳዩን ለማርገብ ጥረት ያደረገው፡፡

የናይጄሪያና የደቡብ አፍሪካ የኢሚግሬሽንና ሌሎች ፍትጊያዎች ከዲፕሎማሲ እይታ አንፃር የብዙዎቹን የአፍሪካ ዲፕሎማቶችና ፖለቲከኞች ቀልብ የሳበ ጉዳይ ቢሆንም ኔፓድን የመሰሉ የኢኮኖሚ ትብብር እሳቤዎች በአፍሪካ አገራት መካከል የሠዎች፣ የሸቀጦች የመረጃና የካፒታል ሠፌ እንቅስቃሴ እንዲኖር እየጠየቁ ባለበት ጉዳዩን መልሶ የመፈተሽን ሥራ የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

## ዶ/ር ዣን ፒንግን ለምን?

ቀጣዩን የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ እንዲህ በጉጉት እንዲጠበቅ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ በህብረቱ ጉባኤ ላይ ከሚነሱት የማሊ የመንግስት ግልበጣና የሶማሊያ ወቅታዊ ሁኔታ አጀንዳዎች ባለፈ ኮሚሽኑን የሚመራው ኃላፊ ማን ይሆን የሚለው ጥያቄ እስካሁን ምላሽ አለማግኘቱ ነው፡፡

ብዙዎች ደቡብ አፍሪካ እንዴት የአብዛኞቹን የአፍሪካ ሀገሮች ድምፅ ማግኘት ተሳናት ለምንስ ጋቦናዊውን ዶ/ር ዣን ፒንግ ለመምረጥ ወሰኑ ብለው ሲጠይቁ ሊያገኟቸው የሚችሉትን ምላሾች ይተነትናሉ፡፡ እንደ ሳይመን አሊስን አባባል ብዙዎቹ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ የአፍሪካ አገራት ከቋንቋ ቅርርብ አንፃርና ምናልባትም ፒንግን እንዲመርጡ ከፈረንሳይ በኩል በተደረገባቸው የማግባባት ሥራ አቋማቸው ወደ ፒንግ እንዳጋደለ ይገልጻሉ፡፡ እንደአሊሰን አገላለፅ ደቡብ አፍሪካ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በአፍሪካ ውስጥ እያንፀባረቀች ባለው ግድየለሽ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባህል ልዕልና የመፍጠር ስሜት አብዛኞቹ አፍሪካውያን ደስተኞች እንዳልሆኑ ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል ደቡብ አፍሪካ ከአፍሪካ አገሮች ጋር ከሁለትዮሽ የፖለቲካ ግንኙነቷ ረገድ የኬንያና የሱዳን ባለሥልጣኖችን የመሰሉ የአፍሪካ ፖለቲከኞች በዓለምአቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ሲከሰሱ አሳልፋ ለመስጠት መወሰኗ ቅሬታውን እንዳባባሰው ይጠቀሳል፡፡ በተያያዘም ደቡብ አፍሪካ ከአብዛኞቹ የአፍሪካ ህብረት አባል አገራትና ከህብረቱ አቋም በተቃራኒ በኮትዲቯርና ሊቢያ ቀውስ ወቅት ላልተገባ ፖለቲከኛ ድጋፍዋን ማንፀባረቋ እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡ በኮትዲቯር ስልጣናቸውን በምርጫ ያጡትን ሎረን ባግቦና

በሊቢያ ህዝባዊ አመፅና የኔቶ ወታደራዊ ጥቃት ከሥልጣን የወረዱትንና በኋላም የተገደሉትን ሙህመር ጋዳፊ ደቡብ አፍሪካ ከጎናችሁ ነኝ ስትል መቆየቷ ይታወሳል።

ዶ/ር ድላሚኒ ዙማ እንደግለሰብ አቅሙና ልምዱ ያላቸው በሳል ዲፕሎማት እንደሆኑ ቢነገርም በደቡብ አፍሪካዊነታቸው ብቻ ይህን ዕድል ሊያጡት እንደሚችሉም ሌሎች ይጠቅሳሉ። በመሆኑም እሳቸውን ዕጩ ያደረገው የደቡባዊ አፍሪካ አባል አገራት ስብስብ ሳዴክ ሌላ ተወዳዳሪ አማራጭ የሚያቀርብ ከሆነ ለዣን ፒንግ ብቻ የሚሉ አገሮች አቋማቸውን ሊለውጡ እንደሚችሉና የደቡብ አፍሪካ ድርቅና ካልሆነ በስተቀር በሳዴክ ከሚገኙ 15 አባል አገራት መሀከልም ዕጩ የሚሆን ተወዳዳሪ እንደማይጠፉ ይገልጻሉ። በዚህ ረገድ ናይጄሪያ የምትመራው የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ስብሰባ ኤኮዎስ ሌላ ዕጩ የሚያቀርብ ከሆነ ያለምንም ጥርጥር ደቡብ አፍሪካ ተሸናፊ እንደምትሆንም ዲፕሎማቶች ይጠቅሳሉ።

ለብዙዎች ሚስጥር ሊመስል የሚችል ለብዙዎች ደግሞ ገሀድ የሆነ ጉዳይ ተብሎ የሚነገረው ብዙ አፍሪካውያን ደቡብ አፍሪካ በአህጉሩ ካላት የኢኮኖሚ የበላይነት አንፃር አሜሪካ በአንዳንድ አገራት የምታሳየውን መሰል ራስ ወዳድ የግድየለሽና ጋጥወጥ ዲፕሎማሲ እያራመደች ነው ብለው ያምናሉ።

በተለይም ደቡብ አፍሪካ በሊቢያና ኮትዲቯር ላይ ያንፀባረቀችው አቋም በብዙ የአፍሪካ ተንታኞች ዘንድ ተነቅፏል። በአዲስ አበባ የሚገኘው የደህንነት ጥናት ተቋም Institute for security Studies የአፍሪካ የግጭቶች ማስወገጃ ፕሮግራም ኃላፊ መሀሪ ታደሰ እንደሚሉት በደቡብ አፍሪካና በአፍሪካ ህብረት መሀከል ከላይ በተጠቀሱትና ሌሎች የደቡብ አፍሪካ Go it Alone የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ምክንያት ብዙዎች ደቡብ አፍሪካን በአፓርታይድ ትግል ወቅት ሲረዱ የቆዩና ቀጥሎም በማንዴላና ምቤኪ ወቅት ወዳጅ የነበሩ አገራት በአገሪቱ ላይ የነበራቸው እምነት መሸርሸር መጀመሩን ይጠቅሳሉ። በመሆኑም ደቡብ አፍሪካ የህብረቱን ኮሚሽን ለመምራት እስከ ደም ጠብታ መታገሏ ከዚህ ቀደም ያልታየና አሁን ለአንድ ዓላማ የታለመና የአገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለማስፈፀም ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው በሚል የብዙ አፍሪካውያን ዲፕሎማቶችና ፖሊቲከኞች ዕምነት የተነሳ ዶ/ር ድላሚኒ ዙማ አሁንም የድምፅ አብላጫ ያገኛሉ የሚለውን ተስፋ ያቀዛቅዘዋል።

ናይጄሪያን ጨምሮ ሌሎች የአፍሪካ ታላላቅ አገሮች ያልተፃፈውን የህብረቱን ልማድ በማክበር ለሊቀመንበርነት ዕጩ ከማቅረብ እራሳቸውን ሲገቱ ደቡብ አፍሪካ ድንገት

አጋጣሚውን በመጠቀም ዕጩ ማቅረቧና ይህንን ልማድ መስበሯ አንድም ልማድ አጥፊ ያሰኛታል አንድም ሌሎች አገራት እኛም እያለን የአንቺ ብቻ ውድድር ለምን የሚል ጥያቄን ያስነሳል። ደቡብ አፍሪካ የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ኃያልነቱ አለና ሌሎች አፍሪካውያንን ለመምራት ድንገት ደረስኩ ከምትል በእርግጥ የአፍሪካውያን ሁሉ ድጋፍ አለኝ ወይ ብላ ዞራ መመልከት ይገባታል ይላሉ መህሪ ታደሰ።

በሌላ በኩል በእንግሊዙ የቻታም ሀውስ የአፍሪካ ፕሮግራም ኃላፊ የሆኑት አሌክስ ቫይንስ እንደሚገልጹት ቀጣዩን የኮሚሽነር ምርጫ ውጤቱን መተንበይ እጅግ አዳጋች ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የደቡብ አፍሪካ ወቅታዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በእርግጥ አንድ የፖለቲካ አጀንዳ ያነገበ ምናልባትም ወደፊት በአፍሪካ ህብረት ፖለቲካ ጥላ ሥር የአገሪቱን የተመድ ፀጥታው ምክር ቤት መቀመጫ የማግኘት ፍላጎት ሊያንፀባርቅ ይችላልና አሁንም ይህ ለአንጋፋ አፍሪካውያን አገራት ደስታን አልሰጠም። ይህ ቢሆንም በተለይ ግብፅን፣ አልጄሪያን እና ሊቢያን የመሰሉ የአህጉሪቱ ኃያላን በአረብ አብዮት ታምሰው ሙሉ በሙሉ ያልተረጋጉ በመሆናቸው እንዲሁም ናይጄሪያ በጎሣና ኃይማኖት አለመግባባቶች መታመስ መጀመሯ ወደፊትም ቀውስ ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮች በርካታ ከመሆናቸው አንፃር አሁንም ደቡብ አፍሪካ ድምጹን ማግኘት ባትችልም በአፍሪካ ህብረት ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪነቷን ትቀጥላለች ሲሉ አልክስ ቫይንስ ይተነብያሉ።

ሌላ የደቡብ አፍሪካን ዕጩ ማቅረብ በግልፅ እንደማትደግፍ ያሳወቀች አገር ብትኖር ኬንያ ነች። በአፍሪካ ህብረት አሠራር ኮሚሽኑን የሚመሩ ሊቀመንበርና ም/ሊቀመንበር ከእንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አገሮች መሆን ይኖርባቸዋል። የወቅቱ ም/ሊቀመንበር ኬንያዊው ኢረስተስ ምዌንቻ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ አገር ኬንያ በመሆናቸው ሊቀመንበርነቱ በደቡብ አፍሪካ የእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገር ዕጩ የሚሸፈን ከሆነ ወዲያውኑ ምዌንቻ ከውድድሩ እንዲወጡ ይደረጋሉ። በዚህ ምክንያት ኬንያ ሁኔታውን ካላት የራሷ ብሔራዊ ጥቅም አንፃር አለመቀበሏን በፕሬዚዳንቷ ሙዋይ ኪባኪ በኩል አሳውቃለች።

የኬንያ የአስተዳዳር ጥናት ተቋም ዳይሬክተር የሆኑት ሙኪሳ ኪቱይ ጉዳዩን አስመልክቶ ለአገሪቱ መገናኛ በቅርቡ በሰጡት መግለጫም ደብብ አፍሪካ ለህብረቱ በምትከፍለው ከፍተኛ መዋጮ ምክንያት የአህጉሪቱ የክርስትና አባት ሆና ለመቅረብ መሞከር አይኖርባትም። በመሆኑም የህብረቱን አንድነት አደጋ ላይ መጣል አይኖርባትም ሲሉም ሀሳባቸውን አቅርበዋል።

## የኢትዮጵያስ ምርጫ

*ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም ተወዛጋቢ ቡድኖችን ወደ ሠላማዊ አንድነት እንዲመጡ የማገባባቱን ሥራ በመሥራት ለድርጅቱ መመሥረት ትልቅና ከፍተኛ ሚና በወቅቱ መሪዋ ኃይሌ ሥላሴ በኩል እንደተጫወተች ይታወሳል፡፡*

*አገሪቱ ከአልበሽር ክስ ጋር ተያይዞ ስብሰባውን ማላዊ ማስተናገድ ባለመቻሏ በጽ/ቤቱ መቀመጫ መልሳ እንድታስተናድግ መጠየቁን ተከትሎም ስብሰባውን ለማስተናገድ ሙሉ አቅሙና ዝግጁነቱ እንዳላት አሳውቃለች፡፡ ኢትዮጵያ ስብሰባውን ከማስተናገድ ባለፈም በህብረቱ ውስጥ ከሊቀመንበሩ ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ መሟሟቶችና መፋተጎች እራሷን ጠብቃ ለህብረቱ አንድነት የሚረዱ አቋሞችን እንደምታንፀባርቅ ይጠበቃል፡፡*

*የአሁኑ የህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ምርጫ የራሱን አደጋ ይዞ መጥቷል፡፡ ዶ/ር ዙማም ሆኑ ዶ/ር ፒንግ ተመረጡ የአፍሪካ ህብረት በጉዳዩ ላይ አንድ ተቋማዊ አቋም የሌለው ይልቁንም የ54 የተለያዩ አገሮች የተለያዩ አቋሞች የሚንፀባረቅበት ብሎም ለውጭ ኃይሎች ፖለቲካዊ ፍላጐት የተጋለጠበትና ወደፊትም በተመሳሳይ ሊያጋልጥ የሚችሉ ክፍተቶችን እያሰፋ ሊሄድ ይችላል፡፡ የአፍሪካ ህብረት በተናጠል የአባል አገራት ፍላጎት ምክንያት ብቻ አንድነቱ ተሸርሽሮ ጥያቄ ውስጥ የገባበት አጋጣሚ ተፈጥሯል፡፡*

*በዚህ ረገድ ለችግሩ እልባት እንዲያፈላልጉ ከተመረጡ የአፍሪካ መሪዎች አንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ከደቡባዊ አፍሪካ አባል አገራት ስብሰባ ሳዴክ የመጣውን የልዑክ ቡድን ባነጋገሩበት ወቅት የገለጹት ጉዳይ ቢኖር አባል አገራት የአህጉራዊውን ድርጅትና የአህጉሪቱን ፍላጐት ማስቀደም እንደሚኖርባቸው እንጂ በተናጠል በብሔራዊ ፍላጎት ዙሪያ ብቻ ታጥሮ በአፍሪካ ህብረት ውስጥ መንቀሳቀስ እንደማይገባ አስገንዝበዋል፡፡ በእርግጥ ይህ በሳል ጥበብ ነው፡፡ አፍሪካን በዚህ ጉዳይ መከፋፈሉ ለመጪው ተመራጭ ሊቀመንበር ሥራም አመቺ ሁኔታን አይፈጥርም፡፡ በዚህ ረገድ የህብረቱን ኮሚሽን ለመምራት ፀሐፊው አዲስ ተወዳዳሪ ዕጩ ቢቀርብ የሚለውን የብዙዎች ሀሳብ ይደግፋል፡፡*

*በዝሆኖቹ ጥል ምክንያት የአፍሪካ ህዝብ እንደ ሣሩ ሆኖ መጎዳትን አይሻም፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ከዚህ እይታ አንፃር የጀመረችውን ተግባር አጠናክራ እንደምትቀጥል ይጠበቃል፡፡ ሠላም፡፡*

***ፀሐፊውን በሚከተለው የኢሜይል አድራሻ ማግኘት ይቻላል :– n_tedla@yahoo.com***